## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን

## ETHIOPIAN AGRICULTURAL AUTHORITY

# የእንስሳት መኖና መኖ ተቋማት ቁጥጥር እና አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ መመሪያ ቁጥር XXX/2018

# Animal Feed Control and Administrative Measures Directive No. XXX/ 2026 .

ግንቦት 2018 ዓ.ም

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

**May 2018**

**Addis Ababa, Ethiopia**

| | |
|---|---|
| **መግቢያ** | **Preamble** |
| የእንስሳት መኖ ምርት ጥራት እና ደህንነት ለማረጋገጥ ከምርት ጀምሮ ጥቅም ላይ እስከሚውል ድረስ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤ | **WHEREAS,** it is necessary to establish a robust control system for animal feed products, from the point of production to the point of utilization, in order to ensure quality and safety; |
| በእንስሳት መኖ ምርት እና ንግድ በተሰማሩ ድርጅቶች ላይ የቁጥጥር ሥራዎች በማጠናከር ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ የእንስሳት መኖ ምርት ለተጠቃሚው ተደራሽ እንዲሆን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤ | **WHEREAS,** it is necessary to establish procedural systems to strengthen inspection and control activities over business entities engaged in the production and trade of animal feed, thereby ensuring that safe and quality animal feed products are made accessible to the consumer; |
| ህገ-ወጥ የእንስሳት መኖ ምርት አመራረትን፣ ስርጭትንና አጠቃቀምን በመከላከልና በመቆጣጠር የእንስሳትን ፣የማሕበረሰብንና የአካባቢን ደህንነት ማስጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤ | **WHEREAS,** it is necessary to prevent and control the illegal production, distribution, and utilization of animal feed products in order to safeguard the health and safety of animals, the community, and the environment; |
| የመኖ ንግድ ተቋማት የመልካም አመራረት ሥርዓት እና የመልካም ንጽህና አጠባበቅ ሥርዓት እንዲከተሉ በማድረግ የእንስሳት መኖ በሰው፣ በእንስሳትና በአካባቢ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት መከላከልና መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤ | **WHEREAS,** it is necessary to prevent and control the harm posed by animal feed to human, animal, and environmental health by ensuring that feed business establishments adhere to Good Manufacturing Practices (GMP) and Good Hygienic Practices (GHP); |
| የመኖ ምርት ተቆጣጣሪዎች ተግባርና ኃላፊነታቸውን ወጥነት ባለው እንዲወጡና ሊወሰዷቸው የሚችሉት አስተዳደራዊ እርምጃዎች ግልፅ ፣ፍትሀዊና ተገማች እንዲሆኑ ለማስቻል የአሰራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ<br>በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በእንስሳት መኖ ምርት ና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀጽ 28(2) መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል። | **WHEREAS,** it is necessary to establish a procedural system to enable feed inspectors to carry out their duties and responsibilities in a |

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ

1. **አጭር ርእስ**

ይህ መመሪያ "የእንስሳት መኖ ምርትና ተቋማት ቁጥጥር እና አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ መመሪያ ቁጥር -----/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

2)**ትርጓሜ**

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004 ውስጥ የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1 ) **"የእንስሳት መኖ ምርት** ማለት የተቀነባበረ መኖ፤የመኖ ጥሬ እቃ፤የመኖ ተጨማሪ ንጥር ነገር እና ማሞያ መኖን የሚያካትት ነው፤

2 ) **"ተቆጣጣሪ"** ማለት በእንስሳት መኖ ምርት እና በእንስሳት መኖ ምርት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራን ሰው በወጣ መስፈርትና ሕግ መሰረት የቁጥጥር ተግባር እንዲያከናውን የሚመደብ ባለሙያ ነው፤

3 ) **"ዘረመሉ የተለወጠ ወይም ልውጥ ሕያው የመኖ ግብዓት"** ማለት በዘመኑ የዕፅዋትና እንስሳት ርቢ ምህንድስና፣በሰው ሠራሽ ዘዴ ከሌላ ሕያው የተወሰደ ወይም

consistent manner, and to ensure that any administrative measures to be taken are clear, fair, and enforceable;

Accordingly, the Ethiopian Agricultural Authority has issued this directive based on Article 28(2) of the Veterinary Drug and Feed Administration and Control Proclamation No. 728/2011.

## Section one

## General Provisions

**1) Short Title**

This directive may be cited as "Directive on the Animal Feed Control and Administrative Measures Directive No. XXX/2026.

2)**Definition's**

Subject to the definitions provided in the Veterinary Drugs and Animal Feed Administration and Control Proclamation No. 728/2004, unless the context otherwise requires, in this Directive

**1)"Animal Feed Product"** means processed feed, feed raw materials, feed additives, and supplement feeds

**2) "Inspector"** means a professional assigned to carry out regulatory and inspection activities on persons engaged in animal feed production and animal feed trade in accordance with the established standards and applicable laws.

| | |
|---|---|
| እንደ አዲስ የተቀመመ ባይተዋር ዘረ መል ወይም ሌላ ንጥረ ነገር የተጨመረበት የዘረ መሎች ይዘት፣ አቀማመጥና ባህርይ የተለወጠበት ሕያው የእንስሳትና የዕፅዋት ውጤት የሆነ የመኖ ግብዓት ነዉ፤ | **3) “Genetically Modified (GM)”**Feed Ingredient means an animal or plant product whose genetic make-up and/or gene sequence has been modified through modern plant and animal genetic engineering that involves the transfer of genes from another living organism or artificially developed or gene modification through addition of foreign entities. |
| 4 ) **“ከአመንዣጊ እንስሳት ምርት የተገኘ የመኖ ግብዓት”** ማለት የሚያመሰኩ እንስሳት እንደ የዳልጋ ከብት፣ጎሽ፣በግ፣ፍየል፣ግመል እና የመሳሰሉት የተፈጨ ሥጋ፣ የደም፣የአጥንት፣ የአንጎል፣ የአንጀት እና ሌሎች ምርት ዉጤት ነዉ፤ | **4) Feed ingredient of ruminant origin**” means a feed ingredient made of by-products of ruminant (Cattle, Buffaloes, sheep, Goats, etc.) slaughter, like meat meal, blood meal, bone meal, brain tissue, intestine products. |
| 5 )**“የመኖ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃ ገላጭ ጽሑፍ”** ማለት በመኖ ወይም በመኖ ጥሬ ዕቃ መያዣ ዕቃ ላይ የሚጻፍ ወይም የሚለጠፍ ወይም የሚታሰር ሆኖ ስለመኖዉ ወይም የመኖ ጥሬ ዕቃው ዓይነት፣የንጥረ ነገር ይዘት፣ለምን ዓይነት እንስሳት አመጋገብ እንደሚዉል፣የተመረተበት ቀን፣የአጠቃቀም አገልግሎቱ የሚያበቃበት ቀን፣የአያያዝና ክምችት ሁኔታ የሚገልጽ ነዉ፤ | 5) **“Feed or Feed Raw Material Label”** means any written, printed, attached, affixed, or tied information on the container or package of feed or feed raw material that indicates the type of feed or feed raw material, nutrient or ingredient composition, animal species for which it is intended, date of manufacture, expiry date, and conditions for handling and storage. |
| 6 )**“ደረጃ”** ማለት በኢትዮጵያ የወጣውን ወይም ሀገሪቷ የተቀበለችው የጥራት እና ደህንነት ደረጃ ነው | 6) **Standard”** means a quality and safety standard issued in Ethiopia or adopted by the country. |
| 7 )**“ሌሎች ተቆጣጣሪዎች “** ማለት የመንግስት ተቋም ሲሆኑ ባለስልጣኑ | 7) **“Other Regulators”** means government institutions and other relevant bodies that work in collaboration with the Authority to facilitate |

| | |
|---|---|
| ጋር የቁጥጥር ስራ ለማሳለጥ የሚሰሩ ባለድረሻ አካላትን ያካትታል፤ | and carry out regulatory activities. |
| 8 )**“የእርምት ማስታወቂያ”** ማለት ባለስልጣኑ በቁጥጥር ወቅት የተገኘ ክፍተት በጣም አንስተኛ ሲሆን እንዲስተካከል ለእንስሳት መድኃኒት ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማራ ድርጅት ወይም ባለሞያ የሚሰጥ የጽሁፍ ግንኙነት ነው፡፡ | 8)"**Correction Notice"** means a written communication issued by the Authority to an entity or professional engaged in the animal feed trade business, requiring the rectification of a very minor deficiency identified during inspection; |
| 9) **“የቃል ማስጠንቀቅያ”** ማለት በእንስሳት መኖ ምርት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ድርጅት በቁጥጥር ወቅት የተገኘበትን የአሰራር ክፍተት በመኖ ጥራትና ደህንነት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት አነስተኛ ከሆነ እና ክፍተቱን ያስተካክላል የሚል በቂ ዕምነት ሲኖር በባለስልጣኑ ማስጠንቀቅያ መስጠቱን ለመግለጽ በጽሁፍ የሚሰጥ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤ | 9) “**Verbal Warning”** means an administrative measure issued by the Authority in writing to an organization engaged in animal feed production or trade, where a procedural deficiency identified during an inspection has a minor impact on feed quality and safety, and there is sufficient assurance that the organization will correct the deficiency. |
| 10) **“የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ”** ማለት በእንስሳት መኖ ምርት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ድርጅት ላይ በቁጥጥር ወቅት ጥፋት ሲገኝበት ያለበትን የአፈጻጸም ክፍት እና ማስተካከያን በተመለከተ በጽሁፍ የሚሰጥ አስተዳደራዊ እርምጃ ነው፤ | 10) **Warning Letter”** means an administrative measure issued in writing to an organization engaged in animal feed production or trade when a non-compliance is identified during an inspection, specifying the performance deficiencies and the corrective actions required. |
| 11) **“ዕገዳ”** ማለት የእንስሳት መኖ ምርት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ተቋም ወይም ባለሙያ በፈፀመው ጥፋት ምክንያት ስራውን | 11) **Suspension”** means an administrative measure taken by the Authority to prohibit an institution or professional engaged in animal feed production or trade from carrying out its activities for a period of up to four months due to an offence committed by the institution or professional |

እስከ አራት ወር ድረስ እንዳይሰራ ለማድረግ በባለስልጣኑ የሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ነው፤

12) “ስረዛ” ማለት የእንስሳት መኖ ምርት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ተቋም ወይም ባለሙያ ወይም የመኖ ምርት ምዝገባ በዚህ መመሪያ ላይ በተቀመጡ ምክንያቶች ለሁለት ዓመት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ወይም ምዝገባን እንዳይሰራ ወይም ጥቅም ላይ እንዳይውል የማድረግ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤

13) “**ክልከላ**” ማለት መስፈርት ባለመሟላቱ ምክንያት የሙያ ፈቃድን፣ የብቃት ማረጋጫ ምስክር ወረቀትን ወይም የመኖ ምርት ምዝገባን ወይም የዕድሳት አገልግሎትን መከልከል ነው፤

14) ”**ተቋማት**” ማለት ማንኛውም በእንስሳት መኖ ምርት ንግድ ላይ የተሰማራ አምራች ወይም አስመጪ ወይም ላኪ ወይም ክልል ተሻጋሪ ጅምላ አከፋፋይ ወይም የማስተዋወቅ ስራ ድርጅት የሚሰራ ነው፤

15) “**ቅሬታ መስማት**” ማለት ማንኛዉም ተገልጋይ በተወሰደበት አስተዳደራዊ እርምጃ ላይ ቅር ከተሰኘ በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ ተመርኩዞ ምላሽ የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ነዉ፤

16) "**ማቆየት**" ማለት በመኖ ምርት ላይ ጥርጣሬ ሲኖር ወይም በተለያዩ አስተዳደራዊ

12) “**Cancellation**” means an administrative measure taken to cancel the certificate of competence or registration of an establishment, professional or feed product registration for a period of two years for reasons set out in this Directive.

**13) "Denial"** means the rejection of a professional license, certificate of competency, or feed product registration or renewal service due to failure to meet the requirements of the authority

**14) “Organization**” means any manufacturer, importer, exporter, trans regional wholesaler, or distributor engaged in the trade of animal feed production which has been granted certificate competence.

**15) “Complaint Hearing"** It is a system where any customer who is dissatisfied with an administrative action taken will be replied to based on the complaint they submit.

**16) "Quarantine"** means keeping the animal feed production out of use when there is doubt about it or due to various administrative measures

**17)** "**Holding** " It is an administrative measure taken when animal feed are illegally

| | |
|---|---|
| እርምጃዎች ምክንያት የመኖ ምርቱ ጥቅም ላይ እንዳይዉል ለይቶ እንዲቀመጥ ማድረግ ነው፤<br>17) "**መያዝ**" ማለት ሕገወጥ የእንስሳት መኖ ምርት በሚጓጓዝበት ወቅት ወይም በመጋዘን ውስጥ ተከማችቶ ሲገኝ የሚወስድ አስተዳደራዊ እርምጃ ነዉ፤<br>18) "**ማስወገድ**" ማለት በሰዎች፣ በእንስሳት እና በአከባቢ ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ለመከላከል ጊዜ ያለፈበትን፣ ጥቅም ላይ የማይውልን፣ ከደረጃ በታች የሆነ እና የተበከለ መኖ ምርትን ጥቅም ላይ እንዳይዉል ማድረግ ነዉ፤<br>19) "**ነጻ ናሙና** " ማለት የእንስሳት መኖ ምርት ንግድ የሚያከናውን ድርጅት ለማስተዋወቅ በነጻ ለተጠቃሚዎች የሚያሰራጨው አነስተኛ መጠን ያለው የእንስሳት መኖ ምርት ነዉ፤<br><br>20) **"የመኖ ምርት ጤና ምስክር ወረቀት"** የመኖ ምርት ጤናማ ስለመሆኑና መኖዉን ለሚመገበዉ እንስሳ ወይም የእንስሳዉን ምርት ዉጤት በሚመገበዉ አካል ላይ የጎንዮሽ የጤና ጉዳት እንደማያስከትል የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ነዉ፤<br><br>21) **"መግቢያና መውጫ ኬላ"** ማለት የእንስሳት መኖ ምርት ወደ አገር የሚገባበትና ከአገር የሚወጣበት በባላስልጣን መስሪያ ቤቱ የሚሰየም መቆጣጠሪያ ጣቢያ ነው፤<br>22) "**ባለሥልጣን**" ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ነው፡፡ | transported or stored in an unauthorized<br><br>18) **"Disposal"** means the safe and proper disposal of expired, unused, substandard, counterfeit, and contaminated feed to prevent them from causing harm to humans, animals, and the environment.<br><br>19) **"Free Sample"** means a small quantity of an animal feed product distributed free of charge by an organization engaged in animal feed trade for the purpose of promoting the product to consumers.<br><br>20) **"Feed Product Health Certificate"** means a certificate that confirms that a feed product is safe and does not cause adverse health effects to the animal consuming the feed or to any person consuming products derived from such animals.<br><br>21) **"Entry and Exit Checkpoint"** means a control station designated by the Authority through which animal feed products enter into or leave the country.<br><br>22) **"Authority"** refers to the Ethiopian Agricultural Authority<br><br>23) **"Customer"** A person who requests a service in order to exercise his/her right to receive a service provided by the authority |

23) “ተገልጋይ”ማለት በባለስልጣኑ የሚሰጥ አገልግሎትን የማግኘት መብት ለመጠቀም አገልግሎት የሚጠይቅ ሰው ነው።

24)በእንስሳት መድሐኒት እና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004 ውስጥ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

3) **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በእንስሳት መኖ ምርት ንግድ በተሰማራ ተቋም ወይም ባለሙያ ወይም በእንስሳት መኖ ላይ በሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

### አጠቃላይ ድንጋጌና የቁጥጥር ተግባር

**4)አጠቃላይ ድንጋጌ**

ማንኛውም በእንስሳት መኖ ምርት ንግድ የተሰማራ ድርጅት ፡-

1. ባለስልጣኑ ባስቀመጠው መመሪያ መሰረት እየሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ይደረግበታል፤
2. ባለስልጣኑ ያወጣቸውን የቁጥጥር አዋጅ፤ ደንብ፣ መመሪያ ካላከበረ እንደ አግባብነቱ በዚህ መመሪያ መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፤
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት

24) Definitions given in the Veterinary Drug and Feed Administration and Control Proclamation No. 728/2004 shall also apply to this Directive.

**3) Scope**

This Directive shall apply to institutions or professionals engaged in the animal feed production and trade business, as well as to administrative measures taken in relation to animal feed.

**Section Two**

**Control, Obligations of the feed product institution and Professionals**

**4( General**

**Any organization engaged in the animal feed production and trade business shall:**

1. Be subject to inspection to verify that it is operating in accordance with the guidelines established by the Authority;
2. Where it fails to comply with the laws, regulations, and guidelines issued by the Authority, be subject to appropriate administrative measures in accordance with this Guideline;
3. Any person against whom an administrative measure has been taken pursuant to Sub-Article 2 of this Article

| | |
|---|---|
| አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት ሰው ቅሬታውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡ | may submit a complaint to the Authority. |
| **5) ቁጥጥር ስለማድረግ** | **5) Regulatory Inspection** |
| የባለስልጣኑ ተቆጣጣሪ የእንስሳት መኖ ምርት ጥራቱ እና ደህንነቱ ለማረጋገጥ በመደበኛ ድንገተኛ ፣ስጋት ፣ተኮር ወይም የክትትል ቁጥጥር በሚያከናውንበት ወቅት እንደ አስፈላጊነቱ የሚከተሉትን ማከናወን አለበት፡- | The Authority's Inspector shall, as necessary, undertake the following activities when conducting routine, unannounced, risk-based, or follow-up inspections to ensure the quality and safety of animal feed products: |
| 1) በእንስሳት የእንስሳት መኖ ንግድ ድርጅት ማምረቻ ወይም ማከማቻ ወይም ማሰራጫ በመግባት ወይም ፈቃድ በተሰጠው የእንስሳት መኖ እና ባለሙያ ላይ በስራ ሰዓት በቦታው በመገኘት ቁጥጥር ማድረግ፡፡ | 1) Conducting inspections by entering the manufacturing, storage, or distribution premises of animal feed organization, or by being present on site during working hours at a licensed animal feed organization and professional. |
| 2)በስራ ሰዓት የእንስሳት መኖ ምርትን የተከማቸበት መጋዘንን ወይም የጫነን ማጓጓዣ በማስቆም የቁጥጥር ተግባር ማከናወን፤ | 2) Conduct inspections during working hours by stopping and inspecting vehicles transporting animal feed products or accessing warehouses where animal feed products are stored and produced; |
| 3)የመኖ ምርቱ በተቀመጠው መስፈርት እና ሰነዶቹ ላይ በተገለፀው መረጃ መሠረት መሆኑን የማረጋገጥ | 3) Verify that the feed product complies with the prescribed standards and conforms to the information provided in the relevant documents; |
| 4)የመኖ ምርት ገላጭ ጽሁፍ ያሉ መረጃዎች የተሟሉ ስለመሆናቸው መቆጣጠር | 4) Verify that all required information on the feed product label is complete and accurate; |
| 5)በመኖ ምርት ማሸጊያ ላይ የሚገኘው መረጃ በምዝገባ ከተሰጠው መረጃ ጋር | 5) Verify that the information provided on the |

| | |
|---|---|
| ተመሳሳይ ስለመሆን አለመሆኑ ማረጋገጥ | feed product packaging is consistent with the information submitted and approved during product registration. |
| 6) የመኖ ምርት ማሸጊያቸው በአግባቡ የታሸገ፣ ምርቱን የማይነካና ለብልሽት የሚዳርጉ ጉድለቶችን ለመከላከል ብቃት ያለዉ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | 6) Verify that the packaging of the feed product is properly sealed, does not adversely affect the product, and is sufficiently durable to prevent defects that may cause damage or deterioration |
| 7) የመኖ ምርት በተገቢ የአጫጫን ሁኔታ በሚፈለገው የጭነት ደህንነት ስለመጓጓዙ መቆጣጠር | 7) Control that the feed product is transported under appropriate loading conditions and in compliance with the required cargo safety standards; |
| 8) የእንስሳት መኖ ምርቶች ከሌሎች ዕቃዎችና ቁሳቁሶች ጋር በጥቅል እንደዳልተጓጓዙ ማረጋገጥ፣ | 8) Ensure that animal feed products are not transported in bulk together with other goods and materials |
| 9) ተገዝቶ ወደ ሀገር ውስጥ የገባው የመኖ ምርት መጠን በግዥ ትእዛዝ ፈቃድ ከተሰጠው መጠን አለመብለጡን ማረጋገጥ፣ | 9) Verify that the quantity of the purchased feed product imported into the country does not exceed the quantity authorized in the purchase order permit. |
| 10 ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት በተደረገዉ ምርመራ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲኖሩ ናሙና በመውሰድ በላብራቶሪ ምርመራ እንዲደረግ የማድረግ እና የላብራቶሪ ውጤት እስኪታወቅ ድረስ የመኖ ምርቱ ተለይቶ እንዲቆይ የማድረግ፣ | 10) Where suspicious conditions are identified during the inspection conducted pursuant to Sub-Article 2 of this Article, take samples for laboratory analysis and ensure that the feed product is segregated and held until the laboratory results are available. |
| 11) ሕገ ወጥ የመኖ ምርት ንግድና ዝውውር በተመለከተ መረጃ ወይም ጥቆማ ሲደርሰው የምርቱን ሕጋዊነት፣ ጥራትና ደህንነት ለማረጋገጥ የመያዝ ፡፡ | 11) Upon receiving information or a report concerning the illegal trade or distribution of |

6) የመኖ ምርትን ስለመያዝና ማቆየት

1) ተቆጣጣሪው በወጡ መስፈርቶች እና ሕጎች የተቀመጠ አሰራርን ሳያሟላ የተገኘ የመኖ ምርት እንዲያዝና ወይም እንዲቆይ ሲያደርግ ይህንን መመሪያና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የቁጥጥር ሕጎችን ማክበር አለበት፤
2) ባለስልጣኑ በወጡ መስፈርቶች እና ሕጎች የተቀመጠ አሰራርን የማያሟላ የመኖ ምርት እንዲቆዩ ወይም እንዲያዙ ሲያደርግ እንደ አግባቡ ከሌሎች የመንግስትና የግል ተቋማት ጋር በጣምራ መስራት ይኖርበታል፤
3) በእንስሳት እና በሰው ጤና እንዲሁም በአካባቢ ደህንነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል የታወቀ የመኖ ምርት ተቆጣጣሪው የመኖ ምርት እስከሚወገድ ወይም ሌላ አግባብ ያለው አስተዳደራዊ እርምጃ እስከሚወሰድ ድረስ ተይዞ እንዲቆይ ማድረግ አለበት፤
4) በቁጥጥር ጊዜ የመኖ ምርት በማቆየት ወይም በመያዝ ሂደት ቁጥጥር የሚደረግበት ተቋም መደበኛ የሥራ እንቅስቃሴ እንዳይስተጓጎል ተቆጣጣሪው አስፈላጊውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት ይኖርበታል፤

feed products, take appropriate measures to detain the product in order to verify its legality, quality, and safety.

**6) Detention and Holding of Feed Products**

1 ) When an inspector seizes or detains a feed product that does not meet the requirements of applicable standards and laws, the inspector shall comply with this Directive and other relevant control legislation

2) When the Authority causes non-compliant feed products to be detained or seized, it shall, as appropriate, work in coordination with other government and private institutions.
**3)** Where it is established that a feed product may pose a risk to animal or human health or environmental safety, the inspector shall ensure that the feed product is detained and held until it is disposed of or another appropriate administrative measure is taken.
4) During an inspection, the Inspector shall have the responsibility to take the necessary precautions to ensure that the normal business operations of the establishment under inspection are not disrupted by the detention or seizure process.
5) Where there is suspicion that any feed

5) ማንኛውም የመኖ ምርት የጥራትና የደህንነት ችግር እንዳለበት ጥርጣሬ ሲኖር ተቆጣጣሪው የመኖ ምርት እንዲቆይ የማድረግ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፤

6) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) እንደተጠበቀ ሆኖ አጠራጣሪ የመኖ ምርት ሲኖር የመኖ ምርት ጥራትና ደህንነት ያለ ላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት የማይታወቅ ከሆነ ተቆጣጣሪው የመኖ ምርት በማቆየት የመኖ ምርት ናሙና በናሙና አወሳሰድ መመሪያ መሠረት ወስደው ለላቦራቶሪ መላክ አለበት፤

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ቁጥጥር የሚደረግበትን የመኖ ምርት የላብራቶሪ ውጤት ለማሳወቅ በባለስልጣኑ ላብራቶሪ አሰራር መሰረት ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፤

8) የላብራቶሪ ምርመራ ውጤት ከታወቀ በኋላ ወይም የመጨረሻ ምርመራ ሪፖርት ከተገኘ፣ ባለስልጣኑ ቁጥጥር ለሚካሄድበት ድርጅት የመጨረሻ ውሣኔውን ከሶስት የሥራ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በደብዳቤ ማሳወቅ አለበት።

**7) ናሙና አወሳሰድ እና የላብራቶሪ ውጤት ማሳወቅ**

1) የመኖ ምርቱ በተፈለገው ሁኔታ

product has a quality or safety problem, the Inspector shall take measures to detain the feed product.

6) Without prejudice to Sub-Article (5) of this Article, where a suspicious feed product exists and its quality and safety cannot be determined without laboratory analysis, the Inspector shall detain the feed product, take samples in accordance with the Sampling Standard Protocols, and submit them to the laboratory.

7) Without prejudice to Sub-Article (6) of this Article, the laboratory results of the feed product under inspection shall be communicated and acted upon in accordance with the laboratory procedures of the Authority

8) After the laboratory test results are available or the final inspection report has been issued, the Authority shall notify the organization subject to inspection of its final decision in writing within no more than three working days.

**7) Sampling and Notification of Laboratory Results**

**1)** Where there is a suspicion that the feed product does not meet the required specifications, inspectors shall, as necessary, collect samples for laboratory analysis**.**

**2)** The quantity of the feed product sample to

| | |
|---|---|
| ስለመገኘቱ ጥርጣሬ ሲኖር እንደ አስፈሊጊነቱ ተቆጣጣሪዎች ለላብራቶሪ ምርመራ ሂደት ናሙና ይውሰዳሉ፤<br>2) የሚወሰደው የመኖ ምርት ናሙና መጠን እንደሚከተለው ይሆናል፡-<br>ሀ. የመኖ ምርቱ ፕሪሚክስ ከሆነ ዱቄት/ጠጣር ድብልቅ ከሆነ ከእያንዳንድ ባች 1ኪ.ግራም<br>ለ. የመኖ ምርቱ ፕሪሚክስ ፈሳሽ ድብልቅ ከሆነ ከእያንዳንዱ ባች 250ሚ.ልትር.<br>ሐ. የመኖ ምርቱ የተቀነባበረ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ ከሆነ በመኖ ናሙና በደረጃ አወሳሰድ እና ላቦራቶሪ መስፈርት መሰረት ይሆናል፡፡<br>3) የላቦራቶሪ ምርመራ ሂደቱ በባለስልጣኑ ላቦራቶሪ ከሆነ ውጤቱ በ20 የስራ ቀናት ውስጥ ለድርጅቱ ይገልፃል፡፡<br>4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 የተቀመጠ የጊዜ ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ ናሙናው ከባለስልጣኑ ላቦራቶሪ ዉጪ ወደ ሌሎች ላቦራቶሪዎች የተላከ ከሆነ ግን በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 3 ከተጠቀሰው ጊዜ በተጨማሪ 15 የስራ ቀናት ውስጥ ውጤቱ ይገለፃል፡፡<br>8)የተቋማት ግዴታ<br>ማንኛውም ተቋም<br>1) በመንግስት የስራ ሰዓት ክፍት | be taken shall be as follows:<br>**a.** Where the feed product is a premix in powder or solid form: 1 kg shall be collected from each batch.<br>**b**. Where the feed product is a premix in liquid form: 250 mL shall be collected from each batch.<br>**c**. Where the feed product is processed feed or feed raw material: the sample quantity shall be determined in accordance with the applicable feed sampling standard and laboratory requirement<br>**3)** Where the laboratory analysis is conducted by the Authority's laboratory, the test results shall be communicated to the organization within 20 working days.<br>4) Without prejudice to the time limit prescribed under Sub-Article 4 of this Article, where the sample is sent to a laboratory other than the Authority's laboratory, the results shall be communicated within an additional 15 working days beyond the period specified under Sub-Article 3 of this Article.<br>**8) Organizational commitment**<br>Any organization<br>1) It should be open to the public during working hours and shall provide services to |

| | |
|---|---|
| በመሆን ለተጠቃሚ አገልግሎት መስጠት አለበት፤ | consumers. |
| 2) የሙያ ፍቃድ የተሰጠው ባለሙያ ሊኖረው ይገባል፤ | 2) It should have a licensed professional. |
| 3) የባለስልጣኑ ተቆጣጣሪ ከእንስሳት መኖ ምርት ሥራ ጋር የተዛመደ ማንኛውንም መዛግብት፣ ሰነድ፣ ማዘዣ፣ ኮምፒውተር መመልከትና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ኮፒ ተደርጎ እንዲሰጠው የመተባበር ግዴታ አለበት፤ | 3) It should Cooperate with the Authority's inspector by allowing inspection of any records, documents, orders or computers related to animal feed activities and, where necessary, provide copies; |
| 4) ስለአመረተው ወይም ስለ ገዛው ወይም ስለአሰራጨው መኖ ምርት እና ሌሎች ተዘማጅ መረጃዎችን በየሶስት ወር ለባለስልጣኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፤ | 4) It should report to the Authority, every three months, information regarding the feed products it has produced, purchased, or distributed, as well as other relevant information. |
| 5) የተከለሰ ወይም የተበላሸ ወይም በማስመሰል የቀረበ ወይም የተበከለ ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚ ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ በተጠረጠረ የእንስሳት መኖ ምርት ላይ የጥራት ምርመራ እንዲካሄድ የማድረግ እና ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስ ምርቱን ማቆየት እና ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፤ | 5) It should conduct quality tests on feed products suspected of being adulterated, spoiled, counterfeited or contaminated or for any other reason likely to cause harm to consumers and shall retain them until the results are known; and notify the Authority.. |
| 6) የመኖ ምርት ጥራት አና ደህንነት ለማረጋገጥ የመኖ ምርት ተቆጣጣሪዎች ናሙና ለመውሰድ በሚጠይቁበት ጊዜ የመተባበር ግዴታ አለበት፤ | 6) It should cooperate with the authority's inspector to inspect any records, documents, prescription computers related to the feed products trade and to provide copies there of when necessary |
| 7) የአገልግሎት ዘመኑ ያበቃ ወይም | 7) Animal feed product that have expired, or substandard, or not registered, or are prohibited from use under this Directive must be disposed of in accordance with the relevant directives or |

| | |
|---|---|
| ከደረጃ በታች የሆነ ወይም ያልተመዘገበ ወይም በዚህ መመሪያ መሠረት ጥቅም ላይ እንዳይውል የተወሰነበትን የእንስሳት መኖ ምርት አግባብ ባለው መመሪያ መሰረት እንዲወገድ ወይም ወደመጣበት ሀገር እንዲመለስ ማድረግ አለበት፡፡ | returned to the country of origin. |
| 9) **የባለሙያ ግዴታ** | **9). Obligations of Professionals** |
| ማንኛውም በባለስልጣኑ የሙያ ፍቃድ የተሰጠው የእንስሳት መኖ ምርት ባለሙያ የሚከተሉት ሀላፊነት እና ግዴታ አለበት | Any animal feed professional licensed by the Authority shall have the following responsibilities and obligations: |
| **1) በምርት ክፍል ኃላፊነትና ጥራት ቁጥጥር ተቆጣጣሪ ባለሙያ** | **1) Professional in charge of the Production Unit and Quality Control** |
| ሀ.) ፍቃድ ከወሰደበት የእንስሳት መኖ ምርት ድርጅት ውጪ መስራት የለበትም፡፡ | a) He/she Shall not work outside the animal feed production establishment for which he/she holds a license; |
| ለ ). ተገቢ የሆነ የስራ ልብስ የመልበስ፤ | b) He/she Shall wear appropriate work attire; |
| ሐ ) ማንነቱን፣ ሙያውንና የስራ ድርሻውን የሚገልፅ የደረት ባጅ የማድረግ፤ | c) He/she Shall display a chest badge indicating his/her identity, profession, and scope of work; |
| መ ) የተሰጠውን ስራ በራሱ የማከናወን፤ | d) He/she Shall perform the assigned duties personally. |
| ሠ) ባለሙያው በማይኖረበት ጊዜ ባለስልጣኑን በማስፈቀድ እና ከድርጅቱ ጋር በሚደረግ ስምምነት መስፈርቱን በሚያሟላ ባለሙያ ከሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ ተክቶ እንዲሰራ ሊያደርግ ይችላል፤ | e) In the absence of the professional, the establishment may, with the approval of the Authority and through an agreement with the establishment, arrange for a qualified professional who meets the prescribed requirements to serve as a substitute for a period not exceeding three months. |
| ረ.) በውክልና ወቅት ስለወከለው ባለሙያ ሙሉ መረጃ የመያዝ፤ | f) To Maintain complete information and records regarding the professional who serves |
| ሰ) በድርጅቱ ክፍሎች በመግባት ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን የመቆጣጠር፤ | |

| | |
|---|---|
| ሽ) ስለ እያንዳንዱ ባለሙያ የስራ ድርሻና ኃላፊነት የሚገልጽ ሰነድ የማዘጋጀት፤<br>ቀ) ባለሙያዎቹ የእንስሳት መኖ ምርት ጥራትና ደህንነትን በሚመለከት ተጨማሪ ክህሎት ሊያገኙ የሚችሉበትን ስልጠናዎች እንዲያገኙ የማመቻቸት፤<br>በ) የሚወጡ አገር አቀፍ ደረጃዎችንና መመሪያዎችን የመተግበርና የማስተግበር፤<br>ተ) የክምችት ክፍሉን ቁጥጥር በተመለከተ በተገቢዉ መንገድ መከናወኑን የማረጋገጥ፤<br>ቸ) የማከማቻ ቦታዎችን ለሚያፀዳ ሰው ሊያጋጥሙት ስለሚችሉ አደጋዎች የማሳወቅ፤<br>ኀ) የባለስልጣኑን እና ሌሎች ተያያዥ መመሪያዎች መሠረት በማድረግ ጥቅም ላይ የማይውሉ የመኖ ምርት በጊዜውና በአግባቡ እንዲወገዱ የማድረግ፤<br>ነ. በእንስሳት መኖ ምርት ጥራት እና ደህንነትላይ ችግር መኖሩን ወይም ጥርጣሬ ሲኖረው ለባለስልጣኑ የማሳወቅ<br>ኘ. ድርጅቱን የሚለቅ ከሆነ ከመልቀቁ አንድ ወር በፊት ለባለስልጣኑ እና ለድርጅቱ የማሳወቅና ፈቃዱን የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡<br>2) **ረዳት የቴክኒክ ወይም የመጋዘን ኃላፊ ሆኖ የሚሰራ ባለሙያ** | as a substitute during the period of delegation.<br>g) To Access the different sections of the establishment and inspect documents related to the provision of services<br>h.) To prepare a document specifying the duties and responsibilities of each professional.<br>I) To facilitate training opportunities for professionals to acquire additional skills related to the quality and safety of animal feed products.<br>J) To implement and enforce applicable national standards and guidelines.<br>K. To ensure that the inspection and control of the storage area are carried out appropriately.<br>l) To inform persons responsible for cleaning storage areas about the potential hazards they may encounter.<br>m) To ensure that feed products unfit for use are disposed of properly and in a timely manner in accordance with the Authority’s requirements and other relevant guidelines.<br>n) To notify the Authority whenever there is a quality or safety problem, or a reasonable suspicion of such a problem, concerning an animal feed product.<br>o) If he intends to leave the establishment, notify both the Authority and the establishment at least one month before leaving and return the professional license. |

| | |
|---|---|
| 1) ተገቢ የሆነ የስራ ልብስ የመልበስ፤<br>2) ማንነቱንና፣ የስራ ድርሻውን የሚገልፅ የደረት ባጅ የማድረግ፤<br>3) በማንኛውም የስራ ሰዓት በድርጅቱ የማከማቻ ክፍል የመገኘት፤<br>4) በድርጅቱ ውስጥ በተሰጠው የስራ ድርሻ መሠረት አገልግሎት የመስጠት፤<br>5) ማከማቻ ክፍል ለሚገባ ወይም ለሚወጣ የእንስሳት መኖ ምርት የገቢና ወጪ የመረካከቢያ ሰነድ ወይም ደረሰኝ በማዘጋጀት ከአስረካቢ ወይም ከተረካቢ አካላት ጋር በመፈራረም ሰነዱን በአግባቡ የማያዝና ለተቆጣጣሪዎች የማሳየት፤<br>6) ባለስልጣኑ የሚያወጣቸው መመሪያዎችንና የአሰራር ስርዓቶችን የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት አለበት፤<br>7) ባለሙያው በማይኖረበት ጊዜ ባለስልጣኑን በማስፈቀድ እና ከባለሃብቱ ጋር በሚደረግ ስምምነት መስፈርቱን በሚያሟላ ባለሙያ ከአራት ወር ላልበለጠ ጊዜ ተክቶ እንዲሰራ ሊያደርግ ይችላል፤ | **a) professional working as an assistanttechnical (warehouse) manager**<br>1) To wear appropriate work clothes.<br>2) To have a chest badge indicating his identity and job role.<br>3) To be present in the organization's storage area at any working hours<br>4) To Provide services in accordance with the duties and responsibilities assigned within the establishment<br>5) To prepare an incoming and outgoing handover documents ፤ record or receipt for animal feed products entering or leaving the storage area, have it signed by the delivering or receiving party, properly maintain the records, and make them available to inspectors upon request.<br>6) To implement with rules, regulation and directives issued by the authority<br>7) In the absence of the professional, he should be replaced by a qualified professional for a maxium period of four months with the approval of the authority and in agreement with the owner. |

| | |
|---|---|
| 8) ድርጅቱን የሚለቅ ከሆነ ከመልቀቁ አንድ ወር በፊት ለባለስልጣኑ እና ለድርጅቱ የማሳወቅና ፈቃዱን የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡ | 8) ) If he leaves the organization, he must notify the authority and the organization one month before leaving and he should return his license |
| **10) ክልከላ** | **10)Prohibitions** |
| 1) ፍቃድ ከወሰደበት የእንስሳት መኖ ድርጅት ውጪ መስራት የለበትም፤<br>2) በማረካከቢያና በክምችት ክፍል ዉስጥ መብላት፣ መጠጣት፣ ሲጃራ ማጨስ ወይም ሌሎች ንፅህናቸው ያልተጠበቁና አላስፈላጊ ተግባራትን አለማከናወን፡፡ | 1. A professional shall not work outside the animal feed establishment for which the licence was issued;<br>2. Eating, drinking, smoking or engaging in other unhygienic or unnecessary activities inside the handover and storage sections is prohibited. |
| **ክፍል ሶስት** | **Part Three** |
| **አስተዳደራዊ እርምጃ** | **Administrative Measures** |
| **11) አስተዳደራዊ እርምጃ** | **11) Administrative Measures** |
| ማንኛውም በእንስሳት መኖ ምርት ንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ፣ ባለሙያ ወይም የመኖ ምርት ባለሥልጣኑ ያወጣቸውን መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ወይም የወጡ መስፈርቶችና መመሪያዎች ጥሰ ከተገኘ እንደ አግባብነቱ የሚከተሉት አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡- | Any person, professional or feed product establishment engaged in the animal feed trade that fails to meet the requirements issued by the Authority or is found in violation of applicable standards and directives may, as appropriate, be subjected to the following administrative measures: |
| 1) የእርምት ማስታወቂያ<br>2) የቃል ማስጠንቀቂያ፣<br>3) የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ፣ | 1. Corrective notice;<br>2. Verbal warning;<br>3. Warning letter;<br>4. Sealing of the feed manufacturing |

| | |
|---|---|
| 4) የመኖ ማምረቻ/መጋዘን እሽጋ፣<br>5) ዕገዳ፤<br>6) ስረዛ፤<br>7) ክልከላ፣ ምርትን ማቆየት፣ መያዝ፣ ማስወገድ፣<br>8) ከገበያ መሰብሰብ፣ ወደ መጣበት ሀገር መመለስ እና<br>9) በወንጀል ለማስጠየቅ አስተያየት መስጠትን ያጠቃልላል፡፡<br><br>**12) የእርምት ማስታወቅያ**<br><br>1) ባለስልጣኑ በሚከተሉት ምክንያት በእንስሳት መኖ ምርት ንግድ ለተሰማራ ተቋም ወይም ባለሙያ እንደአግባብነቱ የእርምት ማስታወቅያ ሊሰጥ ይችላል፡<br>ሀ) የአየር እርጥበትና ሙቀት መለኪያ መሳሪያ ከሌለው ወይንም የተበላሸና አገልግሎት የማይሰጥ ከሆነ፤<br>ለ) የመኖ ምርት ተጠቃሚዎች ቅሬታ ማስተናገጃ ስርአት ከሌለው፤<br>ሐ) የሙቀት መቆጣጠሪያ መለኪያ መሳሪያ፣ዲጂታል ቴርሞ ሜትር እና ሪከርድ ከሌለዉ፤<br><br>መ) ድርጅቱ በባለስልጣኑ ለቁጥጥር አገልግሎት የወጡትን አስፈላጊ የአሰራር መመሪያዎች ከሌለዉ፤<br>ሠ) ባለሙያዎው በስራ ሰዓት የደንብ | plant/warehouse;<br>5. Suspension;<br>6. Cancellation;<br>7. Prohibition, detention, seizure and disposal of products;<br>8. Market recall and return to the country of origin; and<br>9. Recommendation for criminal prosecution<br><br>**12) Notice of Correction**<br><br>The Authority shall take the following administrative measures, as appropriate, against an Institution or a professional engaged in the feed product business, or on the feed product itself:<br><br>a)Where it does not have a humidity and temperature measuring device, or where the device is damaged or non-functional;<br><br>b) Where it does not have a system for handling complaints from feed product consumers;<br><br>c) Where it does not have a temperature monitoring device, digital thermometer, or temperature records;<br><br>d)Absence of necessary operational directives issued by the Authority for inspection services;<br>e. Failure of the professional to wear the |

| | |
|---|---|
| ልብሱን ካልለበሰ፤ | prescribed uniform during working hours; |
| ረ) ለቀጠራቸዉ ባለሙያዎች የስራ ሠዓት መቆጣጠሪያ ከሌለዉ፤ | f. Absence of a time attendance system for employed professionals; |
| ሰ) የሰራተኞች ወይንም የመጋዘን ወይም የመኖ ማምረቻ ቦታ ወይም አጠቃላይ የግቢ ንጽህና ጉድለት ከታየ፤ | g. Observed deficiencies in the hygiene of staff, warehouse, manufacturing area or the overall premises; |
| ሸ) በመጋዘኖቹ ወይንም በማምረቻ ክፍል ውስጥ ተባዮች፤ አይጦች ወይንም ወፎች ከታዩ፤ | h. Presence of pests, rodents or birds in the warehouses or manufacturing section |
| 1) የእርምት ማስታወቂያ የሚሰጠው የቁጥጥር ሥራ እንዳለቀ ወዲያውኑ ሲሆን ማስታወቂያው በቁጥጥር ቼክ ሊስት ላይ በጽሁፍ ሆኖ ቁጥጥር በሚደረግበት ተቋም ባለሙያ ወይም ባለቤት እና በተቆጣጣሪው መፈረም አለበት፤ | 1) The notice of correction shall be issued immediately after the inspection work is completed and the notice shall be in writing way in inspection checklist and it should be signed by both parts. |
| 2) የእርምት ማስታወቅያ የተሰጠው ተቋም በእርምት ማስታወቂያው ላይ ለመፈረም ካልተገኘ ወይም ፍቃደኛ ካልሆነ ተቆጣጣሪው አካል በድርጅቱ በር ላይ መለጠፍ ይችላል፡፡ | 2) If the organization to which the notice of correction issued is not available or is unwilling to sign, the inspector should post it on the door of the organization |
| 3) የእንስሳት መኖ ንግድ ድርጅቱ በታዘዘው የጊዜ ገደብ መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፤ | 3) The organaization shall be responsible for implementing the necessary corrective actions in accordance with the prescribed timeline. |
| 4) የባለሥልጣኑ ተቆጣጣሪ አስፈላጊው ማስተካከያ መደረጉን ለማረጋገጥ ተገቢውን የክትትል ሥራ መስራት አለበት፡፡ | 5) The Authority's inspector shall carry out appropriate monitoring to ensure that the necessary corrections are made. |
| | 6) Failure by the organization to make the necessary corrections within the prescribed time limit pursuant to sub-article 4 of this article shall be sufficient reason for issuing a verbal warning |

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 መሰረት ድርጅቱ በታዘዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስፈላጊውን ማስተካከያ ካላደረገ የቃል ማስጠንቀቂያ ለመስጠት በቂ ምክንያት

**13) የቃል ማስጠንቀቂያ**

1) ባለስልጣኑ በሚከተለው ምክንያት በእንስሳት መኖ ምርት ንግድ ለተሰማራ ተቋም ወይም ባለሙያ እንደአግባብነቱ የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠቱን ለመግለጽ በጽሁፍ ሊሰጥ ይችላል፡-

ሀ) የተበላሸ እና አገልግሎት ጊዜ ያለፈበት መኖ ምርት ለይቶ የሚያስቀምጥበት ቦታ እና ሪከርድ ከሌለዉ፤

ለ) የአገልግሎት ጊዜ ያለፈበት የእሳት መጥፊያ ይዞ ከተገኘ፤

ሐ) ለቀጠራቸዉ ባለሙያዎች የስራ ሠዓት መቆጣጠሪያ ከሌለዉ፤

መ) የተቋሙ ባለሙያዎች ያለ ፍቃድ ወይም ያለውክልና ወይም አሰማኝ ምክንያት በአንድ የቁጥጥር እና የክትትል ጊዜ በስራ ገበታው ካልተገኘ፤

1) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የቃል ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ተቋም በታዘዘው የጊዜ ገደብ መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ የማድረግ እና

**13) Verbal Warning**.

